

# ምድራዊ የብርሃንና የትንሳኤ ሀገር ኢትዮጵያ

*<<ጽድቁንና መንግስቱን ፈልጉ ሌላው ይጨመርላችኋል።>>ከኀጢያትና ከሀሰት ስራ በቀር ሁሉ ተፈቅዶልናል።*

**የሀሰት አባት ልጆች በሙሉ ቀኑ መሸባችሁ!!**

## ማውጫ


ምዕራፍ አንድ፡ የሰው ልጅ የመኖር መርህና ዓላም ምንድን ነው? .......... 2

ከዚህ እውነት አንድ ነገር መረዳት ይቻላል። .......... 3

የጨለማ ሀገር .......... 3

የብርሃን ሀገር .......... 4

ይህ የህዝብ ዓላማ ወይም መርህ ምንድን ነው? .......... 5

ምዕራፍ ሁለት፡ ሰው ሲኖር በሕይወቱ በሶስት መሰራታዊ ክፍሎች የተወሰነ ነው። .......... 5

አንደኛ በስጋዊ እንቅስቃሴ .......... 5

ሁለተኛው ደግሞ በመንፈሳዊ ስራዎች .......... 6

ሶስተኛው በነፍስ ፈቃድና ስራዎች .......... 6

ስለዚህ የብርሃን ልጆች በዚህች ሀገር ሲኖሩ እንዲህ ነው። .......... 7

መዕራፍ ሶስት፡ የዚህች የብርሃን ሀገር ሶስት ዓበይት የዓለት መሰረቶች፣ አስራ ሁለት ደግሞ ምሰሶዎች/ግድግዳዎች እና የተዋበና ያጌጠ ከዳን ወይም ጣራ አሏት። .......... 8

ሶስቱ የዓለት መሰረት የተባሉት .......... 8

አስራ ሁለቱ ምሰሶዎች/ግድግዳዎችስ .......... 8

1. መገበያያ ገንዘብ ሳይሆን መኖሪያና መተዳደሪያ ሕጋዊ አገልግሎት .......... 8
2. እውነተኛና ግልፅ መረጃ .......... 10
3. የፍትሕ ቦታዎች .......... 10
4. የሐይማኖት ተቋማትና አገልጋይ አባቶች ወይም እናቶች .......... 10
5. የመንግስት አስተዳደር ቦታዎች .......... 11
6. ማሕበራዊ ሕይወት .......... 11
7. ትምህርት ቤቶች .......... 11
8. የተፈጥሮና የሰው ልጅ ግኑኝነት .......... 11
9. ጊዜን መለኪያና መቁጠሪያውን በትክክል ማወቅ .......... 11
10. የራስን መክሊት ፈልጎ ማግኘት .......... 12
11. ለእውነተኛው አምላክ በእምነት ዘወትር ምስጋና ማቅረብ .......... 12
12. ፍቅር ለፈጣሪ ለሰው ልጅ ለእንስሳት እንዲሁም ለፍጥረታት በሙሉ .......... 12

አንድ የብርሃን በርና አስራ ሁለት ድንቅ መስኮቶች ያሏት .......... 12

የተዋበና ያጌጠ ከዳኗስ .......... 12

ማጠቃለያ .......... 13

## ምዕራፍ አንድ፡ የሰው ልጅ የመኖር መርህና ዓላም ምንድን ነው?

እስኪ ከጥንቱ ከጥዋቱ እንጀምር፡

አዳም በገነት ሲኖር ከፈጣሪ የተሰጡት ስጦታዎች ምን ምን ናቸው? ጥቂቶቹን እንዘርዝር

1. ምስጋና፡ በሚያየውና በሚሰማው ድንቅ ድንቅ ፍጥረታት በሙሉ የፈጣሪን ስራ ያደንቅ ያመሰግንም ነበር
2. ፍፁም ውስጣዊና ውጫዊ ሰላም
3. ፍቅር ለፍጥረታት ሁሉ እንዲሁም ለአምላኩ
4. እውነት (ማለትም ሀሰትን አያውቅም ነበር ሀሰትን አይናገርም አያደርግም ሌሎች ፍጥረታትም እንዲሁ ናቸው ብሎ ይቀበላል እንጂ ሀሰትን ጭራሽ መኖሯን አያውቅም)
5. ልጅነት፡ የስላሴ ልጅነትን ተቀብሏል። አባቱ ወይም ጠባቂው ፈጣሪው ነው።
6. የዋህነት፡ እንስሳትን ሁሉ በየዋህነቱ ይጠብቃቸው ነበር፡ አርደህ ብላን ሲሉትም መርቆ ይሸኛቸው ነበር።
7. እምነት፡ በገነትም ሲኖር የፈጠረው አምላኩ እንደሆነ አምኖ ምስጋና እያቀረበ እስከሚሳሳትበት ቀን ድረስም ሕጉን እየጠበቀ ኖሯል።
8. ክህነት፡ ከመላእክት ጋ ዘወትር በየጊዜው ምስጋና ማቅረብ
9. ንግስና፡ በመሬት ላይ ለተፈጠሩ ፍጥረታት በሙሉ ንጉስና ገዢ ሆኖ ተሹሟል
10. ትንቢት፡ ሔዋንን እንዳያት ይህች አጥንት ከጥንቴ ስጋዋም ከስጋየ ነውና ሚስት ትሁነኝ ብሎ ስም አወጣላት፣
11. አርአያ ስላሴ፡ አዳምም ሲፈጠር ከ አራት ባህርያተ ስጋና ከረቂቅ ሶስት ባህርያተ ነፍስ ነው።
12. ጸጋ፡ የብርሃን ልብስ፣ የብርሃን ዘውድና አክሊል፣ የብርሃን ጫማ፣ የብርሃን ካባ፣ የብርሃን በትርና የብርሃን ዙፋን፣ የብርሃን ሰረገላ፣ ቅዱስ ቦታና መኖሪያ ገነትን፣ ከፍጥረት ሁሉ መግባቢያ አንድ ቋንቋንና ሌሎችንም

ከዚህ የምንረዳው የሰው ልጅ ከታች በተዘረዘሩት በቁሳዊ ነገሮች እንዲከብር ሳይሆን የተፈጠረው በመንፈሳዊው ሃብት እንዲከብር ነው።

አሁን ሰለጠነ በሚባለው በሰው ስጋዊ ፍላጎት የተሰሩና የተገኙ ለምሳሌ

- ቤት፡ ትልልቅ ህንፃዎችና መኖሪያዎች
- የተለያዩ አልባሳት
- መጓጓዣዎች፡ መኪና፣ መርከብ፣ አውሮፕላን፣ጀት ወይም መርከብ
- የተለያዩ ፋብሪካዎች
- ማህበራዊ አገልግሎት መስጫዎች፡ ት/ቤት፣ሆስፒታል፣ባንክ፣
- መገበያያ ገንዘብና ሌሎችም

እንዲሁም የሰው ልጅ ዓላማ ብሎ በህይወቱ ሲኖር ከነዚህ አንዱን ተከትሎ በዚያ ውስጥ ለመስራትና ለመኖር ማለትም

- ነጋዴ
- ገበሬ
- መምህር
- ኢንጅነር
- ዶክተር
- ግንበኛ
- አናፂ
- ልብስ ሰፊ
- ሜካኒክ
- ቆዳ ልብስና ጫማ አዛጋጅ
- ወታደር
- ሳይንቲስት
- ደላላ
- ተማሪ

ወዘተ

በመሆን ሕይወቱን ይገፋል። አሁን ያለንበትን ዓለም አዳም ከሚኖርበት ጊዜ ማነፃፀር ለሚችል ሰው በአጠቃላይ እነዚህን ያስተውላል።

በአዳም ጊዜ ሰው ሚስጥራዊና መንፈሳዊ የሆነውን ሕይወት በሚገባ ያውቀዋል ነገር ግን በስጋዊ ሕይወት ብዙ ነገር አያውቅም

በአሁኑ ጊዜ ደግሞ የሰው ልጅ በስጋዊ ሕይወቱ በጣም ብዙ ርቀት በመሄድና በመመራመር አሁን የደረሰበት የቴክኖሎጂ ደረጃና የስልጣኔ ደረጃ ደርሷል ነገር ግን በመንፈሳዊው ሕይወቱ ወደ ዜሮ በመሄዱ የፈጣሪ ሕልውና እንኳን ተክዶ ሀሰት በዚህ ዓለም ላይ ነግሷል።

ስጋ በባህርይው ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ያፈራል፣ ይሞታል። ይህ ስጋ ለባሽ የሆነ ፍጥረት ሁሉ የሚያከናውን የሕይወት ዑደት ነው። ረቂቅ የተባለች በስጋ ዓይን የማትታይ ነፍስ ደግሞ የማትሞት ዘላለማዊት ነች።

ስለዚህ በአዳም ጊዜ የሰው ልጅ እድሜው ዘጠኝ መቶ ዓመትና ከዚያ በላይ ነበረ ምክኒያቱም አፈርነቱን ሳይሆን ዘላለማዊነቱን እያሰበ በስጋው ፈቃድ ሳይሆን በነፍሱ ፈቃድ ወይም ግዞት ስለሚኖር ዘላለማዊት የሆነችው ነፍሱ እድሜውንም ታረዝማለች ወደራሷ ለመውሰድ እነ ቅዱስ ሔኖክን ብንወስድ እንዴውም እስካሁን ሞትን አልቀመሰም እድሜው ከ ስድስት ሺህ ዓመታት በላይ ነው ማለት ነው። ፍፁም ሆኖ ለፈጣሪው ፈቃድ በነፍሱ ገዢነት ለሚንቀሳቀስ እውነት እውነት እላችኋለሁ ከእናንተ መካከል ወልድ በጌትነቱ እስኪመጣ ሞትን የማይቀምስ  አለ ብሎ ለሐዋርያት ጌታችን ነግሯቸዋል ቅዱስ ዮሃንስ ወልደ ነጎድጓድን።

በአሁኑ ዘመን ደግሞ አኗኗራችን እንደ ስጋ ፍቃድ ነው። ማለትም ከላይ እንዳየነው አሁን ያለው ዓለም ስልጣኔና ስርዓት በሙሉ የተገነባው በስጋ ፈቃድ እንጂ በነፍሳችን ፈቃድ አይደለም። ስለዚህ ምን ያህል ያወቅን የረቀቅን የሰለጠን ቢመስለንም አኗኗራችን ስጋዊ ነውና እድሜያችንም ስጋዊ ሆነ። ሰባና ሰማንያ ምን አልባት አንዳንዶች እስከ መቶ ሃያና ሰላሳ ዓመታት ሊኖሩ ይችላሉ።

### ከዚህ እውነት አንድ ነገር መረዳት ይቻላል።

ይህም ስጋዊ ሕይወት ፍላጎቱ የማያልቅ ፍፃሜውንም የማያውቅና ሁል ጊዜ ባለመረጋጋትና ውስጣዊ ሰላምን ባለመስጠት ሕይወትን የሚያባክን ነው።

የነፍስ ፍቃዳዊ ሕይወት ደግሞ ፍላጎቱ የተገደበ መረጋጋትና ሰላም ያለው መደምደሚያውንና መቋጫውንም የሚያውቅ ነው።

እስኪ እንስሳትን እንመልከት ከእነርሱ መካከል ስለሚበላው ተጨንቆ የሚያርስ ወይም የሚዘራ አለ? ለልብሱስ ተጨንቆ የሚፈትልና ጨርቅ የሚሰፋ አለ? ቤቱን አሳምሮ በግንብና በሌሎች ማዕድናት አክብሮ የሚሰራ አለ?

ሁሉንም ፍጥረታት ፈጣሪያቸው ይመግባቸዋል ያኖራቸዋል በድንቅ ስራውም አልብሶ ፈጥሯቸዋል። ስለዚህ እነሱ ለምንም አይጨነቁም በፈጣሪያቸው ታምነው ይገባሉ ይወጣሉ።

የሰው ልጅ ግን ከዚህች ከቀላሏ ምሳሌ መማር አቅቶት ነፍሱን ረስቶ በስጋዊ ፈቃዱ ብቻ በማይጠቅመውና በማይረባው ከላይ በዘረዘርናቸው ስልጣኔ ከተባሉ የዘመኑ የስጋዊ ፍቃድ ውጤቶች ብቻ በማተኮርና ያንን ብቻ ሕይወቱ በማድረግ እየኖረ ነው።

ግን ሰው በዚህ ዘመን መኖር የነበረበት/ያለበት እንዴት ነው?

የጨለማ ሀገርና የብርሃን ሀገር በምን ይለያያል? እስኪ ሁሉንም በየተራ እንመልከት

### የጨለማ ሀገር

ጨለማ መጀመሪያ ምንድን ነው ብንል ያማይዳሰስ የማይጨበጥ መንገድ ልሂድ ብንል መሄጃው የማይታወቅ ጠላትን ሌባን እንይ ብንል የማንችል ወዳጅንም እንዲሁ፣ ስራ ሊሰራበት የማይቻል ሊዝናኑበትም የማይቻል ምንም ስራ ሊሰሩበት ሳይሆን በጨለማ ሰው ይተኛል ይህም በአጠቃላይ ጨለማ የሞት ምሳሌ ነው።

ስለዚህ የጨለማ ሀገር ማለት የሞት ሀገር ነው። የት የት አለ ብንል

ይህች ምድር አንዷ ምሳሌ ናት ለምን ቢባል። ሰው ተወልዶ ሲሞት ለምን ተወልድኩ ብሎ እውነትን መርምሮ የተወለደበትን ዓላማ ወይም ምስጋና አድርሶ ተመልሶ ሲያመሰግነው ወደ ነበረው አምላክ በክብር መሄድ ካልቻለ በስጋዊ ምኞቱ ብቻ ሲመላለስ ኖሮ ተመልሶ ከሄደ የኖረበት ሀገር የሚኖርበትም ሀገር ሞት ነው ምክኒያቱም ጨለማን መርጧል።

እስኪ አንድ ነጋዴ በራሱ ሀገር የጨው ሀብት በብዛት ሁሉም ሰው ጋ እያለ ሩቅ ሀገር ሄዶ ጨው በብዛት ገዝቶና ጭኖ ቢመጣ ከሰረ እንጂ የእርሱን ጨው እንኳን ዋጋ ጨምሮ የሚገዛ በዋጋውም የሚገዛው አይኖርም ምክኒያቱም ሁሉም ሰው ጋ አለ ርካሽ ነው። ልክ እንደዚህ ነጋዴም ሰው ተወልዶ እንዲሁ በስጋ ፍቃድ ተመላልሶ ብቻ መሞት ስራው ከሆነ እንደነጋዴው ከሰረ ምክኒያቱም እንስሳት ራሱ እንዲሁ በስጋ ፈቃዳቸው ተመላልሰው ኖረው ይሞታሉ፣ ሰው ከእነርሱ መብለጡን አላወቀም። ይህ ዓለምም መገለጫዋ ይህ ነው በአጠቃላይ።

## የብርሃን ሀገር

ብርሃን ማለት ምን ማለት ነው?

ከስሙ ትርጓሜ ብንነሳ በግዕዝ አ፡በ፡ገ፡ደ፡ሀ፡ወ፡ዘ፡ሐ፡ጠ፡የ፡ከ፡ለ፡መ፡ነ፡ሰ፡ዐ፡ፈ፡ጸ፡ቀ፡ረ፡ሠ፡ተ፡ኀ፡ጰ፡ፀ፡ፐ ቅደም ተከተል አ አንድ ብለን እስከ ፐ ሃያ ስድስት ሲሆኑ

**ብ፡2 ር፡20 ሃ፡5 ን፡14 ድምር 41 ይሆናል።**

ይህም ብርሃን እንዲህ ነው ወይም እንዲህ አይደለም ከማለት በግልፅ ስለሚያስረዳልኝ አሁንም በፊደላት ቀመር እቀጥላለሁ

**እ፡1 የ፡10 ሱ፡15 ስ፡15 ድምር 41 ይሆናል።**

**አ፡ 1 ማ፡ 13 ኑ፡ 14 ኤ፡1 ል፡12 ድምር 41 ይሆናል።**

**አ፡1 ብ፡2 ር፡20 ሃ፡5 ም፡13 ድምር 41 ይሆናል።**

**ሣ፡ 21 ራ፡20 ድምር 41 ይሆናል።**

**ዓ፡ 16 ለ፡12 ም፡ 13 ድምር 41 ይሆናል።**

ከፊደላቱ ቀመር የምንረዳውና የምናስተውለው አንድ ነገር አለ ይህም ፡

ዓለምን በሙሉ ካለመኖር ወደ መኖር የፈጠረ የዓለም ብርሃን የተባለ ጌታችንና መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ አማኑኤል እንደሆነ እርሱም በቃሉ መሰረት አዳምን ለማዳን ከአብርሃምና ከሣራ ከልጅ ልጅ እንደተወለደ ነው።

ተጨማሪ የቅዱሳን መጽሐፍትን ጥቅሶች ማየት እንችላለን

እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ብርሃን ሳለላችሁ ተመላለሱ ይላል በወንጌል ጌታ ይህን ብቻ ብናይ ብርሃንን በሚገባ እንረዳለን።

ስለዚህ የብርሃን ሀገር ማለት የአምላካችንና የመድኃኒታችን የእየሱስ ክርስቶስ ሀገር ማለት ነች። እንዴት እርሱን የምታውቅ(ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ እንደሆነ አምላክ ስጋን ተዋህዶ ሰው እንደሆነ የምታምን፣) እርሱን የምትወድና ሕጉንም የምትፈፅም ያቺ ሀገር የብርሃን ሀገር ትባላላች።

ስለዚህ ቅድሚያ በፀናች ሐይማኖት ላይ የተመሰረተች ሀገር ከዚያ በምግባርና በሕይወት ደግሞ ለሕጉ ተገዢ ሆና ትኖራለች።

ከሁሉ አስቀድሞ ወንጌልን እንደ ሐዋርያት በተግባር እግዚአብሔር በመረጣቸው ሰዎች ብቻ በሀገሪቱ መስበክና ማስተማር ያስፈልጋል። ያለ እርሱ ፈቃድ በራሳቸው ተነሳሽነት የሚሰብኩ ካሉ ወንጀል እንጂ ወንጌልን አይሰብኩም በሐዋርያት ጊዜ

ሰይጣን እራሱ ሐዋርያቱን አውቃቸዋለሁ እናንተ ግን እነማን ናችሁ ብሎ እንደከሰሳቸው ያለመንፈስ ቅዱስ ምርጫ በየትኛውም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ደረጃ መቀመጥ አይቻልም።

በህዝብ ደረጃ ደግሞ አኗኗራችን ሊሆን የሚገባው በመርህና በዓላማ ነው።

### ይህ የህዝብ ዓላማ ወይም መርህ ምንድን ነው?

በ 20 ወይም 30 ዓመታት ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት መግባት? ወይም የበለፀገች ሀገር መገንባት ወዘተ? ይሄ ሁሉ ስጋዊ ፈቃድና ምኞት የፀነሰው ወደ ጨለማ ሀገር የሚመራ ነው።

በብርሃን ሀገር መኖር የሚፈልግ ህዝብ መርሁ ወይም ዓላማው ስወለድ እርቃኔን ሆኘ ምንም ሳይኖረኝ ተወልጃለሁ ስሞትም እንዲሁ ብቻየን ወደ መቃብር እወርዳለሁ የሰራሁት ስራ ብቻ ምስክር ሊሆነኝ አብሮኝ ይወርዳል ስለዚህ ዘወትር ዕለት ዕለት የእግዚአብሔርን መንግስት በማሰብ፣በመሻት፣በመጓጓትና በመጠባበቅ ፅድቅን በመስራት መኖር ይህ ነው የብርሃን ህዝብ ዓላማና መርህ። <<**የእግዚአብሔርን ፅድቅና መንግስት ቅድሚያ ፈልጉ ሌላው ይጨመርላችኋል።**>>

ነገር ግን በጽድቅ የሚመላለስ ሰው ብዙ ፈተናና መከራ ይበዛበታል ለምን ቢባል ስራው ክፉ ሆኖ ሳይሆን በጽድቅ ሳይሆን በክፋት የሚመላለሱ ከፈጣሪ ፈቃድ ይልቅ የአጋንንትን ፈቃድ ለመፈፀም በተሰለፉ ሰዎች ምክኒያት።

ነገር ግን በብርሃን ሀገር መኖር የሚችል ለፈጣሪ ፈቃድ የተገዛ ሰው ብቻ ስለሆነ ጽድቅን መስራት በዚህች ሀገር መከራ ወይም ነውር አይሆንም ክብርና ሽልማት ጌጥም ጭምር እንጂ። ነውር የሚሆነው ክፉ መስራትና የሀሰትን ስራ መስራት ነው።

የዚህችን ምድራዊ የሆነች ሕይወትን ስጋዊውን ከመንፈሳዊ እንዲሁም ከነፍስ የዘላለም መዳረሻዋ ጋ አስማምታ የያዘች የብርሃን ሀገር መገለጫዎቿን ጠቅለል አድርገን እንይ።

- ❖ መገበያያ ገንዘብ በሀገሪቱ የለም
- ❖ ባለጊዜ ወይም ባለስልጣን የለም
- ❖ ሕግ አውጭ፣ አስፈፃሚና፣ ተርጓሚ የለም
- ❖ የኔ ብቻ የሚባል ቦታ ወይም ሀብት የለም
- ❖ የኔ ስራ ይህ ነው ከዚህ ውጭ ሌላ የለኝም አይሰራም

ስናጠቃልለው ሁሉም ሰው ዳኛ ነው፣ፖሊስ ነው፣ገበሬ ነው፣ወታደር ነው፣ጣቢቃ ነው፣ ምስጋና አቅራቢ ነው፣ በእያንዳንዱ የሕይወት እንቅስቃሴ በኃላፊነት ተሳታፊ ነው እንዴት? አብረን እንይ

## ምዕራፍ ሁለት፡ ሰው ሲኖር በሕይወቱ በሶስት መሰራታዊ ክፍሎች የተወሰነ ነው።

### አንደኛ በስጋዊ እንቅስቃሴ

ለሌላ አላማ ሳይሆን ስጋዊ ምኞቱን ለመፈፀም ማለትም ለመብላት፣ለመጠጣት፣ለመልበስ ወዘተ ይወጣል ይወርዳል ስለዚህ ከሚከተሉት በአንዱ የስራ መስክ ይሰማራል

- ❖ ግብርና
- ❖ ብረታ ብረት ስራ
- ❖ የእንጨት ስራ
- ❖ ሽመናና አልባሳት
- ❖ ቆዳ ውጤቶች
- ❖ ሸክላ ስራ
- ❖ መብራት፣ ስልክ፣ውሃ፣መገናኛ ሚዲያዎች

- የቤት የቢሮ የፋብሪካ መገልገያ ማሽኖች ማምረቻ
- ሕንፃ ስራ፣መንገድ ስራ፣ግድብ ስራ፣ መሰረተ ልማት ስራ
- ውትድርና ጥበቃና ፖሊስ ሌሎችም ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች አስተማሪ
- የህክምና ሙያ ባህላዊም ዘመናዊም
- የተለያዩ ፋብሪካዎች፣ የስኳር፣የዘይት፣ዱቄት፣ጨርቃ ጨርቅ ፍራፍሬ ወዘተ
- የገጠርና የከተማ ጽዳት ስራ
- ያገለገሉ እቃዎች ማስወገጃና መልሶ ማምረቻ
- ንግድ ሳይሆን ተቀባይና አድራሽ
- ንብ እርባታ
- መጋቢ/የዕለት እንጀራና መጠጥ አዘጋጅና አቅራቢ/በእንግዳ ማረፊያ ቦታዎችና በስራ ቦታዎች
- ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ
- አስተባባሪ ወይም አስተማሪ

በሌሎችም የስራ መስኮች አንድ ሰው ይሳተፋል።

**ሁለተኛው ደግሞ በመንፈሳዊ ስራዎች**
መንፈሳዊ ሕይወቱ የሚጠይቃቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ በሚከተሉት ውስጥ ይሳተፋል

- የተለያዩ ፓርክና የተፈጥሮ መስህቦችን አስጎብኝ
- ታሪካዊ ስፍራዎችን አስጎብኝ
- ማህበራዊ ሕይወት ሰርግ፣ልቅሶ ወዘተ አስተባባሪ
- ፈረስ ግልቢያ፣ውሃ ዋና፣ ሳይክል፣ በረራ፣ልዩ ልዩ ጨዋታዎችና አስተውሎቶች፣ኳስ ጨዋታ፣ገበጣ ወዘተ አጫዋች
- የተለያዩ የጥበብ ስራዎች፡ ስዕል፣ቅኔ፣ዜማና ግጥም ወዘተ አቅራቢና አዘጋጅ
- አሳቂ/ኮሜዲያንና አስለቃሽ/በርኅሩኅነት

እናም ሌሎችን

**ሶስተኛው በነፍስ ፈቃድና ስራዎች**

የሚሰማራ ሲሆን እነዚህም

- ቅዱሳን መፅሐፍት አዘጋጅ
- የቤተክርስቲያን አልባሳት አዘጋጅ
- ስዕለ አድኅኖ አዘጋጅ
- ቅዱሳን ገዳማትና መካናት አገልጋይ
- እንግዳ ተቀባይ
- ሰባኪ
- ስብሃት አቅራቢ
- ንዋየ ቅድሳት አዘጋጅ
- የቤተክርስቲያን ሕግና ስርዓት አዘጋጅ
- የቆሎ ተማሪና ሌሎችንም

እንግዲህ አንድ ሰው በዚህች የብርሃን ሀገር ሲኖር የመጀመሪያውና መሰረቱ ክርስቶስን መቀበልና ማመን ፍቃዱንም ለመፈፀም ዝግጁ መሆን ነው። አምነው ለተቀበሉ እንኳን ደስ አላችሁ። አምነናል ብላችሁ ግን እርሱንም ሳታውቁ ፈቃዱንም ሳትፈፅሙ በስሙ ለምትነግዱ ደግሞ ወዮታ አለባችሁ። ጭራሹንም ላማታውቁ ደግሞ እወቁት ፈልጉት ሕይወት ነውና ያለ እርሱ

የዘላለም ሕይወት የለምና። ነገር ግን ክርስቶስን በመፃረር የጥልቁን መንፈስ እያመለካችሁና ለከፉ ስራውም እየተገዛችሁ ለምትኖሩ ሁሉ ወዮላችሁ ከአጋንንት ጋ አብራችሁ ትጠፋላችሁ። በዚህች ሀገር እንድትኖሩ ፈፅሞ አይፈቀድላችሁም። ጥላችሁ ውጡ ወይ ደግሞ ኃፍረታችሁንና ቅጣታችሁን ተሸከሚት ከቻላችሁት።

## ስለዚህ የብርሃን ልጆች በዚህች ሀገር ሲኖሩ እንዲህ ነው።

አንድ ሕፃን ልጅ ተወለደ ከዚያም በእናቱና በአባቱ ቤት እስከ አራት ዓመት ያድጋል።

ከዚያም በቤተክርስቲያን ፊደልን ምግባርንና ሐይማኖትን እስከ 12 ዓመቱ ጠንቅቆ ተምሮ ይጨርሳል።

ሁለት ዓመት ደግሞ ከዘመናዊው ትምህርት ይማራል።

ከዚያም በመጀመሪያ በግብርና ስራ አንድ ዓመት ይቆያል

ከዚያም በሌሎች የስራ መስኮች ሁሉ ከአንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ እየዞረ ከሁሉም ስራዎች በቅንነትና በኃላፊነት በመስራትና እያንዳንዱ ስራ ያለውን ኃላፊነት በትጋትና ክብር በመማር 12 ዓመት ሀገርንና ህዝብን ያገለግላል።

አሁን የ 26 ዓመት ወጣት ነው። ስለዚህ ወደፊት በሕይወቴ የምቀጥልባቸው በነዚህ የስራ መስኮች ነው መክሊቴ ነው ብሎ በመረጣቸው ከ ሰባት የስራ መስኮች ያላነሰ ከ 12 የስራ መስኮች ደግሞ ባልበለጠ በመምረጥ ሰባት ዓመት በነዚህ መስኮች በድንብ ያገለግላል ይፈተናልም።

ከዚያም ብቁ ሆኖ በተገኘባቸው ቢያንስ በአራትና ከዚያ በላይ የስራ መስኮች ቀሪውን ሕይወቱን ትዳር ይዞ ቤተሰብ መስርቶ ይገፋል ማለት ነው።

እንዴት ለምሳሌ አንድ ሰው ባስደሰቱትና ብቁ ሆኖ የተገኛባቸው የስራ መስኮች

ግብርና

ሽመና

ትራንስፖርት ሰጪ

ህክምና

ፅዳት

በእነዚህ ብቁ ሆኖ ቢገኝ በእያንዳንዱ ሙያው ህዝብን አንድ አንድ ዓመት ያገለግላል። በየዓመቱም መንፈሳዊ አገልግሎት እንደሁኔታዎች ይሰጣል እርሱም ያገኛል።

በተመሳሳይም ከነፍስ ስራዎች እንደስጦታው ከ 30 ዓመቱ ጀምሮ ማለትም ክህነት፣ምንኩስና፣ምነና መጽሐፍ ሰእለ አድጎኖ አዘጋጅ ወይም ሌላ እንደ ስጦታው ሁሉም ይኖራል።

ይህም የግድ ሁሉም ሰው በየዓመቱ ስራ ዘርፍ እየቀያየረ ይስራ ማለት ሳይሆን መክሊቱ ወይም ስጦታው ያላቸው ለስራውም ብቁ የሆኑ ብቻ ናቸው መስራት ያለባቸው ሌሎች ግን በተሰጣቸው አንድም ሆነ ሁለት መክሊት በቅንነት ማገልገልና ማትረፍ ነው ኃላፊነታቸው።

ነገር ግን ይህን ሁሉ የሚሰራ አንድ ሰው በያዘው በሀገሩ መርህና ዓላማ እንጂ ለገንዘብ ወይም ለዝና አይደለም። ሁሉም ሰው በጊዜው በተቀበለው ሙያ ያለ ክፍያ ህዝብ አገለገለ ማለት እርሱም የሚያስፈልገውን አገልግሎት ከሌሎች አገኘ ማለት ነው።

ሌላው በዚህች ሀገር የታወጁ የእረፍትና የበዓላት ቀናት ይኖራሉ። በእነዚህም ቀናት በታላቅ ክብር ተከብረው ይውላሉ። ዘወትርም ምስጋና አይታጎልም፣ በወግ የሆኑ የጨዋታና የሀገርና ቤተሰብ ጥየቃና ጉብኝት ጊዜም እያንዳንዱ ሰው ይኖረዋል።

## መዕራፍ ሶስት፡ የዚህች የብርሃን ሀገር ሶስት ዓበይት የዓለት መሰረቶች፣ አስራ ሁለት ደግሞ ምሰሶዎች/ግድግዳዎች እና የተዋበና ያጌጠ ክዳን ወይም ጣራ አሏት።

### ሶስቱ የዓለት መሰረት የተባሉት

1. እውነተኛውን ፈጣሪ ማወቅና እርሱንም ብቻ ማምለክ።
2. ጽድቅንና መንግስቱን ፈልጉ ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል።
3. የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው።

### አስራ ሁለቱ ምሰሶዎች/ግድግዳዎችስ

1. **መገበያያ ገንዘብ ሳይሆን መኖሪያና መተዳደሪያ ሕጋዊ አገልግሎት**

በአሁኑ ዘመን አንድ ሰው በኪሱ ወይም በስልኩ ወይም በባንክ አካውንቱ በአጠቃላይ ገንዘብ ባይኖረው ምን ማድረግ ይችላል? ያለ ክፍያ በነፃ ሊያገኘው የሚችለው ነገር ወይም አገልግሎት ምንድን ነው? በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ ምንም ነገር ማግኘት ወይም መጠቀም አይችልም። ምግብም ሆነ ትራንስፖርት ቤትም ሆነ ልብስ ንፁህ ውሃ እንኳን አሁን በሃይላንድ ስም በሽያጭ ሆኗል። ገንዘብ ያለው ይኖራል የሌለው ግን ለጽድቅ ብለው በሚኖሩ ሰዎች ምጽዋት/ስጦታ ይኖር እንደሆነ እንጂ የእለት ጉርሱን እንኳን ቀምሶ ማደር አይችልም።

በቀደሙት አባቶቻችን ዘመን ሲነገር እንደሰማነው መገበያያ ገንዘብ ሳይኖር በፊት ሰው ለክብረ በዓላት፣ንግስ፣ መንገደኛ፣ የመሸበት ወይም ማንም እንግዳ በአካባቢ በቤት ወይም በገዳም ቢመጣ የእግዚአብሔር እንግዳ ተብሎ በክብር እግሩን በሙቅ ውሃ አጥበው ራቱን አብልተው አጠጥተው እንዳይበርደው እሳት አንድደው አልጋውን አንጥፈው አሳድረው በሰላም ይሸኙታል። ለምን አብርሃምን ምሳሌ በማድረግ አብርሃም ዘወትር እንግዳ ስለሚቀበል ሳያውቅ አጋዕዝተ ዓለም ስላሴን ተቀብሏል። ለዚህ ክብር ስለበቃ እንደሱ ክብር ለማግኘት ለጽድቅ ሲሉ እንጂ ትርፍና ወጪ በማስላት ወይም ደግሞ ለገንዘብ ሲሉ አይደለም።

አሁን በኛ ዘመን ግን ይሄ ፈፅሞ አይታሰብም ምክኒያቱም ፍቅር ቀዘቀዘ፣ ሰው ሳይሆን ገንዘብ የተባለ ጣዖት በሰው ሁሉ ኅሊና ነገሰ። ገንዘቡን በሀቅ በላቡ ወጥቶ ወርዶ የሚያገኝ አለ በሌብነትና ጭራሹንም እንዴውም በሕገወጥ መንገድ በማተም በጣም በአቋራጭ መንገድ የሚያገኙትም አሉ። ገንዘቡ አንድ ነው መገበያያ ነገር ግን እንዴት እኩል ዋጋ ሊኖረው ይችላል?

ከፈጣሪና ከዚያ ሰው በቀር ገንዘቡ እንዴት እንደመጣ ለሌላው ሳይታወቅ ወደገበያው ለመገበያየት ይቀላቀላል። ይህም ማለት የጥሩት ፍሬና የጽድቅ ፍሬ ተቀላቀለ ማለት ነው። ግን ሁለቱ ምን ያገናኛቸዋል ጨለማና ብርሃን ኃጢያትና ጽድቅ ምን ህብረት አላቸው??

ለዚህም ነው ሰው ለዚህ ጣዖት ገንዘብ ሲገዛ ኅሊናውን በመሸጥ ገንዘብ ለማግኘት የሚችለውን አቋራጭ መንገድ የሚሄድ ማጭበርበር፣ሙስና ባዕድ ነገር ቀላቅሎ መሸጥ ድለላ ወዘተ በእለት ተለት ኑሯችን የምናውቀው የአደባባይ ምስጢር የሆነ ጉዳይ ነው። የብዙ ሰውም ዓላማ ምንድን ነው ቢባል በእርግጠኝነት ሃብታም መሆን ወይም ብዙ ገንዘብ በቀላሉ በሚገኝበት የስራ መስክ መስራትና የተንደላቀቀ ኑሮ መኖር ነው። ይሄ ደግሞ የብርሃን ሀገር ሳይሆን የጨለማ ሀገር መታወቂያ ነው በአጭሩ።

ነገር ግን በብርሃን ሀገር መገበያያ ገንዘብ የለም። ነገሩ ሊገርም ስለሚችል ጥያቄዎችን ያስነሳል

ታዲያ ሰው ለምን ይሰራል? ምን ጥቅም አገኛለሁ ብሎ ይሰራል?

የሚፈልገውንስ ነገር እንዴት ያገኛል? ምግብ፣ልብስ፣ቤትና ሌሎችንም አገልግሎቶች በሙሉ?

የሚሰራውና የማይሰራውስ እንዴት ሊሆን ነው? በሚሰሩ ሰዎች መካከል እንኳን ልዩነት አለ ስለዚህ ሰው ሁሉ ተመሳሳይ የኑሮ ደረጃ ይኖረዋል ማለት ነው?

ከሚነሱ ጥያቄዎች የተወሰኑትን ካየን  ያለ ምንም አይነት መገበያያ ገንዘብ የሚኖረው ህዝብ እንዴት እንደሆነ በሚገባ ስንረዳ ያኔ የጥያቄዎቻችንን መልሶች እናገኛለንና እንዴት እንደሆነ አብረን እንይ።

በሀገሪቷ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ አንድ ቤተሰብ ማለት ናቸው። ታዲያ እናት ለልጇ ዳቦ ትሸጥላታለችን? ወይስ አባት ለልጁ ልብስ ይሸጥ? ወይም ደግሞ እህት ለወንድሟ ስራ/መንገድ ሲሄድ የቋጠረችለትን ስንቁን ትሸጥለት። ነው ወንድም እህቱን ከእርሷ ጥቅም ፈልጎ እህቱን/እናቱን ይታዘዝ ይርዳ። በጎ ኅሊና ያለው ሰው በአንድ ቤተሰብ ውስጥ መገበያያ ገንዘብ ሳይሆን የሚያስፈልግ መግባቢያ ቋንቋ እንደሆነ ይረዳል። ይህም ማለት ሁሉም የቤተሰብ አባላት በአግባቡ የሚጠበቅባቸውን ስራ በኃላፊነት ይሰራሉ በፍቅር በመከባበርና በመተሳሰብም ይኖራሉ ማለት ነው። ስለዚህ አባትና ህፃን ልጅ እኩል ሰርተው አይውሉም ለሰወኛ። ነገር ግን አባት ቢያርስ ልጅ ደግሞ ቢዘራ ሁሉም የሚችለውን በቅንነት ከልቡ ከሰራ የእድሜ፣የእውቀት ወይም ደግሞ የክህሎት ጉዳይ እንጂ አሁን መስራት ያልቻለውን ስራ በመማር በጊዜው መስራት እንደሚችል ግልጽ ነው። ስለዚህ ሲያረጅ የሚጦረውን ልጁን አሁን በመልካም ስነምግባርና ስብዕና በማሳደግ <<ሳትወልድ ብላ>> ከሚለው ከዘመኑ ብሂል ይልቅ ዓይኑን በዓይኑ ዓይቶ ልጅነቱን ሳይጠግበው አሳድጎ ባጎለማሳነቱ የሚራዳው ሲያረጅ ደግሞ የሚጦረው ይሆናል ማለት ነው።

ስለዚህ አባት የተባለ መንግስት እናት ከተባለችው ሀገር የተገኙትን ልጆች የተባሉ ህዝቧን በኃላፊነት በሕግና በስርዓት መምራት ግዴታው ነው። ይህም ነገ ሀገርን የሚረከቡትን ልጆች በመልካም ስነ ምግባርና የስራ ኃላፊነት በማሳደግ ትውልድ ያፈራል። በሕግና ደንብም የህዝቡን ፍላጎት አቅም፣ችሎታ፣ክህሎትና ስጦታ/መክሊት ባማከለ ሁኔታ ሁሉንም ዚጎቿን ከህፃን እስከ አዛውንት በስራ/በኃላፊነት ቦታ በመመደብ ሁሉም ዜጋ ለአንድ ሀገር ግንባታ በሚችለው እንዲሰራ ያደርጋል። እያንዳንዱ ሰውም የሚኖረው የተሻለ ሕይወት ለመኖርና ለፉክክር ወዘተ ሳይሆን በወጣትነት ዘመኑ በትኩስ ጉልበቱ ሀገሩንና ወገኑን አገልግሎ ነገ ሀገር ተረካቢ ለመሆን የአገልግሎት ዘመኑንም ጨርሶ በስጦታው/መክሊቱን አውቆ በዚያ ስራ ጉልበቱ እስኪዝል ያለ ቀሪ ሕይወቱን በማገልገል የተረጋጋ ሕይወት ለመኖር ነው። ስለዚህ በሀቅና በቅንነት በውጤታማነት ያገለገለበትና ፍሬ ያፈራበት ጊዜ ተመዝግቦና የታሪኩ ምስክር ሁኖ ለቀሪ ህይወቱ ዋስትናና ሞገስ ይሆናል ማለት ነው። ይህም ፍሬ እንደየሰው ስጦታው/ስራው ኃላፊነት ልዩነት እንዳለው ሁሉ የሚያገኛቸው የህይወት አገልግሎት ሽልማቶችና ተጨማሪ ማበረታቻዎች ይኖራሉ ማለት ነው።

ሁሉም ሰው መሰረታዊ የሆኑ የሰው ልጅ ፍላጎቶችን ማለትም ከዕለት ምግብ፣ውሃና ሌሎች መጠጥ፣መብራት፣ልብስ፣መኖሪያ ቤት፣ህክምና፣ትምህርት፣ትራንስፖርት፣በዓመት ፈቃድ የመረጡትን መንፈሳዊ/ታሪካዊም ሆነ የተፈጥሮ ቦታ ለተወሰነ ጊዜ የመጎብኘትና ሌሎችንም የማግኘትና የመገልገል መብቱ ለአንድ አምላኩን አመስግኖ ፍላጎቱን ምኞቱን በመጠን ወስኖ ለቆመለት የብርሃን ሀገር ዓላማና ሕግ ተገዢ ሆኖ ለሚኖር የሀገሪቱ አባል የተጠበቀ ነው። የሰው ልጅ ምኞትና ፍላጎት ግን በተፈጥሮው የተገደበ ስላልሆነ ይህንንም መገደብ ነፃነትን እንደመግፈፍ ሊታሰብ ስለሚቺል በሀገሪቷ የሚኖሩ ሰዎች ያለክፍያ በቋሚና በሚጠበቅባቸው አገልግሎታቸው ብቻ ከሚያገኙት አገልግሎት/ተጨማሪ የሆነ ነገር የሚፈልግ ሰው ካለ ግን መልካም እስከሆነና ከሀገሪቷ ዓላማና መተዳደሪያ ሕግ እስካልወጣ ድረስ ተጨማሪ አገልግሎት በሚችለውና በተማረው ሙያ ከሚሰጠው የእረፍት፣የመዝናኛጊዜ ወይም ሌላ በመቀነስ ከተቀመጠለት ኃላፊነት በተጨማሪ ሌላ በመስራት የፈለገውን ተጨማሪ አገልግሎት/ፍላጎት ያገኛል ማለት ነው። ሃሺሽና ጋንጃ ወይም ጫትና ሲጋራን፣ ከልክ ያለፈና ያለጊዜ ወይም ቦታ የሚጣጡ አልኮሎች(ስካር) መቼም ተጨማሪ ፍላጎት ተብሎ በማንም ሰው እንደማይነሳ ጥርጥር የለውም።

በዚህ አጋጣሚም ከሀገር ውጭ እንዲሁም በሀገር ውስጥም ያላችሁ ገንዘብ ለማግኘት ስትሉ ብዙ መስዋትነት የከፈላችሁ፤ የገንዘብንም ሀይል ስለምትረዱ ያንንም አብዝታችሁ ይዛችሁ ቀሪ ህይወታችሁን ተደላድለን እንኖራለን ብላችሁ ለምታስቡ፦

I. በሀቅና በንፅህና ላመጣችሁት ማለትም ሳረጅ ወይም ስሸመግል መጠሪያየ ይሆናል፣ ለልጆቼም ምን አወርሳለሁ በሚል የዘመኑ ሃሳብና ሌሎችንም ደግሞ እደግፋለሁ ብላችሁ የሰበሰባችሁት ከሆነ ያንን በረከት ማን እንደሰጣችሁ ማንስ መንገዱን ከፍቶ እንደደገፋችሁና ከብዙ ውጣውረድና የፈተና ጊዜያት በኋላ እዚህ እንዳደረሳችሁ ስለምታውቁ የሕይወትን ትርጉም፤ መልካም ዘርቶ መልካም ማጨድን በሚገባ ስለምታውቁ መገበያያ ገንዘብ ቢኖር ባይኖር በእናንተ ሕይወት ምንም ለውጥ የለውም ምክኒያቱም የተሰጣችሁ የሕይወት በረከት እንጂ የሚቆጠር የገንዘብ ብዛት እንዳልሆነ በሚገባ ስለምታውቁ በበረከትና በረዳችሁ አምላክ ፈቃድ መኖር ለምትጀምረው ሀገር አርአያና ምሳሌ በመሆን በደስታ ከዓላማዋ ጋ ትቆማላችሁ። ለዚህም ማራጋገጫችሁ የመሰረታችሁት ሰላማዊና የተረጋጋ በፍቅር የተመላ ቤተሰባችሁ ምሳሌ ነው። ስለዚህ መገበያያ ገንዘብ አለመኖሩ ለእናንተ እንዴውም ትልቅ የኅሊና እረፍት እንደሚሰጣችሁ አምናለሁ ከነዚህ ከሶስቱ አምላካዊ ወቀሳዎች፡

II. በትንሹም ሆነ በገፍ በማጭበርበርና በማታለል የተከማቸ ገንዘብና ሀብት ደግሞ ምክኒያቱ ምንም ይሁን ምን ጥሩም ሆነ በጎ ኅሊናን ሸጦ የመጣ ማለትም የኅሊና ወቀሳ ተጥሶ የመጣ ነው። ስለዚህ ሕግና ደንብ ተሸሮ ወንጀል ተፈፅሞ የመጣ ነው ማለት ነው። ተፀፅቶ ለተመለሰ የሕይወትን ዓላማ በዚህች ሀገር ይማራል ለወደፊቱም ደስተኛ ይሆናል ገንዘብ ብቻ ለሚታየው ግን የሚከተሉትን ሶስት አምላካዊ ወቀሳዎች ብቻ አስቀምጬ ልጨርስ፡

- ❖ ሰው ለሁለት ጌታ መገዛት አይችልም አንዱን ይወዳል ሌላውን ደግሞ ይጠላል። ለገንዘብ ወይም ለእውነተኛው አምላክ ለሁለቱም መገዛት አትችሉም
- ❖ ባለፀጋ በጎተራው ሙሉ ድልብን አከማቸ አብዝቶም ሰበሰበ ከዚያም ነፍሴ ሆይ ለህይወትሽ የሚበቃሽን ሁሉ ለልጆቼና የልጅ ልጆቼ ሁሉ የሚሆን ሀብት ሰብስቤልሻለሁ ብዪ ጠጪ ደስ ይበልሽ ይላል። ነገር ግን የቀረው እድሜ ምን ያህል እንደሆነ የሞት መላእክም ነፍሱን ሊወስድ ከበሩ እንደቆመም አያውቅም። ከፉዎች የሰበሰቡትን ቅኖች ይወርሱታል ይበሉታልም።
- ❖ ሌላውና የመጨረሻው ደግሞ ያ ከልጅነት እስከ እውቀት ድረስ ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቆ የኖረው ባለፀጋ ከልጅነቴ ጀምሬ ሕግን ጠብቄያለሁ ምን ይቀረኛል ብሎ ጌታ እየሱስን ሲጠይቀው ስለ ሕግ ጣባቂነቱ መስክሮለት አንዲት ብቻ እንደምትቀረው ያችም ያለህን ሁሉ ሽጠህ መፅውተህ ተከተለኝ አለው እርሱም በሕይወቴ ሁሉ የለፋሁበትን ብሎ አዘነ፤ ስለዚህ እንዲህ አለ <<ባለፀጋ መንግስተ ሰማያት ከሚገባ ይልቅ ግመል በመድፌ ቀዳዳ ብታልፍ ይቀላል።>>

### 2. እውነተኛና ግልፅ መረጃ

ሀቅን ሳይሸፋፍኑ ማንንም አስተዳዳሪም ሆነ ሹመኛ ሳይፈሩ የህዝብን ጥያቄ በሚገባ የሚያቀርቡ እንዲሁም የመንግስትንም መመሪያ የሚያቀርቡ ከሕግና ደንብ መስፈርት አንፃር የሚገመግሙ እውነተኛ፣ለፍትሕ፣ለፍቅርና በአጠቃላይ ለሀገሪቱ ዓላማ በሀገሪቱ ሕግ የቆሙና የሚያገለግሉ ነፃና ገለልተኛ መረጃ ሰጪና አስተላላፊ ተቋማት እነዚህ የህዝብ ዓይንና ጆሮ ማለት ናቸው።

### 3. የፍትሕ ቦታዎች

ሰው ሲበድልና ሲያጠፋ፣ አለመግባባትም ሲከሰት ወይም ደግሞ ከትንሽ እስከትልቅ ወንጀል ሲፈፀም፤እንደየደረጃው በሽምግልና፣በሐይማኖይ ተቋማት ወይም በመንግስት የፍትሕ መስጫ ተቋማት ሕግ መሰረት ተገቢውን ምላሽ ማለትም የእርምት ሕይወት ሊያገኝ ይገባል። ይህም ለእውነትና ለፍትሕ የሚሰሩ አካላት ኃላፊነት ነው።

በዚህ ውስጥም ጥበቃ፣ፖሊስ፣ወታደር፣ጠበቃ፣ዳኛ፣ሽማግሌ ወይም የሐይማኖት አባት ለቆሙለት ዓላማ በሕጉ መሰረት ለኅሊናቸው ተገዢ ሆነው ያገለግላሉ ማለት ነው።

### 4. የሐይማኖት ተቋማትና አገልጋይ አባቶች ወይም እናቶች

ከስጋዊ ባህርይና ከረቂቅ የነፍስ ባህርይ የተገኘው ሰው የነፍሱ ዓላማና መርህ በስጋ የሚኖረውን ሕይወት ገዝቶ እንዲኖር እውነተኛውን አምላኩን ከማሳወቅ ጀምሮ በቅንነት እስከ ማገልገልና መታዘዝ ድረስ በማድረስ ቀና ትውልድ ማፍራት ኃላፊነታቸው ነው ማለት ነው። አጠቃላይ ስርዓቱም የሰማያዊ መንግስት ምሳሌ እንጂ የፖለቲካ መዋቅር/ፍላጎት አይደለም ዓላማውም ሰማያዊ የሆነች ሀገርን መሻት ልጆችንም ለዚያ ዓላማ አርአያና ምሳሌ እንዲሁም ቸር እረኛ በመሆን ማዘጋጀት ነው። ለዚህም ፍትሐ ነገስት ጋ የተደነገጉት ፍትህ መንፈሳዊ ሕጎችን መረዳትና መተግበር ነው።

### 5. የመንግስት አስተዳደር ቦታዎች

ከታች ከቀበሌ ጀምሮ እስከላይኛው የመንግስት አስተዳደር ድረስ ያሉ የህዝብ አገልጋዮች በቦታው የተቀመጡት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ህዝባቸውን በሚገባ ለማገልገል እንጂ ለወንበርና ለሹመት አይደለም። ሰው ለዚህ ኃላፊነት አንተ ትመጥናለህ ተብሎ ይሾማል እንጂ እኔን ለዚህ ኃላፊነት ምረጡኝ አይልም ያለውን ከባድ ኃላፊነት ስለሚያውቅ ከሞራል ከሕግና ከማህበረሰብ እሴት ተጠያቂነት ለመዳንና በክብር ለማገልገል በተሰጠው ቦታና ጊዜ በትጋት ሰርቶ ቶሎ እረፍትን ለማግኘት የተሻለ እርሱን የሚተካ ሰው ፈልጎ በማስረከብ ቶሎ ለመገላገል ይፈልጋል እንጂ በህዝብ እምባ የራስን ተደላድሎ መኖር አይታሰብም። ወንበሩ የተሰጠው ህዝብ መንግስትን ሊያገለግል ሳይሆን ያ የመንግስት አካል የሆነ አስተዳዳሪ ህዝብን ሊያገለግል ነው። በአጫሩ ለመናገር እረኛ ሆኖ ህዝቡን የሚጠብቅ ማለት ነው። እረኝነት ደግሞ መቼም አይሰለቸኝም የሚል ወይ በጎቹን የሚወድ እውነተኛ እረኛ ነው ወይ ደግሞ በጎቹን አርዶ የሚባላና የሚያወራርድ ደም የለመደ ተኩላ ነው። እውነተኛው እረኛ እስከፈለገና እስከቻለ ቢጠብቅ በጎቹ ደስተኞችም ናቸው ደኅንነታቸውም የተጠበቀ ነው። ተኩላውን ግን ፈጥነው ካላባረሩት በጎቹን እንደሚበትናቸው ግልፅ ነው።

### 6. ማሕበራዊ ሕይወት

ማህበራዊ ሕይወት የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግ፣ቋንቋ፣እሴት፣ስነ ምግባርና ስብዕና የሚመሰርት ነው። ስለዚህ መልካም እስከሆነ ድረስ የአንድ ማህበረሰብ ባህሉ፣ቋንቋው፣እሴቱ በአባላቱ ዘንድ ተጠብቆ ሊኖር ይገባል መለያው ነውና። እንዲሁም የበርካታ ባህል ቋንቋና እሴት ባለቤት የሆነች ሀገር ምን ያህል ውብ እንደምትሆን ላስተዋይ ቀላል ነው ያ ባህል ልምድና እሴት ከሀገሪቷ ዓላማ እስካልተጣረሰና እስካልተጋጨ ድረስ። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ዘመን አመጣሽ ቴክኖሎጂ ዓለም ወደ አንድ ባህልና ልምድ ማለትም ግሎባላይዜዥን በማምጣት በአውሮፓውያን ባዕድና የጨለማ ሀገር ልምድ የኛዋ ሀገርም ከፍተኛ ተፅዕኖ ስር ወድቃለች። ለምሳሌ ያህል፡ በማህበራዊ ሚድያዎች ቲክቶክ፣ቴሌግራም፣ዩቱዩብና ሌሎችም ከኢትዮጵያዊነትም ከስብዕናም ያፈነገጡ በርካታ ነገሮች ይዘዋወራሉ፡፡ ይህ ደግሞ ትውልድን በረጅሙ ቀኝ መግዛት ባህሉንና መሰረቱን በማጥፋት ዘመናዊ ባርነት መዘርጋት ነው። ከዚሁ ሁሉ ጋ ቤቲንግ፣ዳንኪራ ቤትና የዝሙት ቤርጎ ቤት፣ ሃሽሽ ቤትና ሌሎችም በሙሉ በዚህች ሀገር ቦታ አይኖራቸውም። ለተተኪ ትውልድ አርአያ የሚሆንና የሚቀርፅ በወጉና በስርዓቱ በባህላችንና በጨዋ ደንብ የሚካሄድ ማህበራዊ ህይወት ይኖረናል በዲጅታል ዓለሙም ሆነ መሬት ላይ ባለው ማህበራዊ ሕይወት።

### 7. ትምህርት ቤቶች

እነዚህ ተቋማት ትውልድን ማንነቱን የሚቀርፁ ተቋማት ናቸው። ነገር ግን በሀገራችን ያሉ የትምህርት ተቋማት ገሃዱ ዓለም ላይ ያለውን ሕይወት ሳይሆን በምዕናብ የተሳለ ቲወሪ ብቻ በማስተማር ከሰው ልጅ መሰረታዊ የመኖር መርሆች ሰው እንዲያፈነግጥ በማድረግ፣ከኬጂ ወይም መዋዕለ ህፃናት ጀምሮ ጥቅሙ ለማይታወቅ ደረጃ ተማሪዎች እንዲወዳደሩ በማድረግ ለደረጃ እንዲማሩ ተደርጎ የተቀረፀ። አብዛኛውንም የተማሪዎች የሕይወት እድሜ እንዲያባክኑ ተደርጎ ሆን ተብሎ የተቀረፀ በጠላቶቻችን የተዘጋጀ ስርዓት ነው። ይሄ የከሰረ ስርዓት ግን በዚህች ሀገር ስለማይሰራ ደገኛ ስርዓት ለትምህርት ይዘጋጃል። ከላይ በመግቢያው በተወሰነ መልኩ ለመግለጽ እንደተሞከረው።

### 8. የተፈጥሮና የሰው ልጅ ግኑኝነት

ተፈጥሮና ግብርና ለሰው ልጅ የሚየስተምሩት ረቂቅ ትምህርት አለ። ገበሬ አርሶ ዘርቶ ኮትኩቶ እስከ ፍሬ ካደረሰ በኋላ እንደገና አጭዶ ሰብስቦ ወቅቶና አበራይቶ ፍሬውን ከገለባው ለይቶ ወደ ጎተራው ያስገባል። በዚህ ሂደት ገበሬ ከተፈጥሮና ከፈጣሪው ጋ ጥልቅ ግንኙነትና መግባባትን ያውቃል። ዝናብን የሚያዘንብ እርሱ ቢያሳድግ ቢያለመልም እርሱ እንዲያፈራ ቢያደርግ እርሱ አጠቃላይ ያለውን ግንኙነት እንዲህ በትንቢተ ኢሳያስ ምዕራፍ 1፡ ከቁጥር 1 እስከ 31 ያለውን አንባቢ ያንብብ እኔ ግን ቁጥር 19 ጋ ያለውን ቃል እንዲህ አሰፍረዋለሁ። <<እሺ ብትሉ ብትታዘዙም የምድርን በረከት ትበላላችሁ። እምቢ ብላችሁ ብታምፁ ግን ሰይፍ ይበላችኋል>> ይህ በግልፅ እንደሚያስረዳው ከፈጣሪው ጋ የሆነ ህዝብ ተፈጥሮ ሁሉ እንደምትታዘዝለት እምቢ ላለ ደግሞ ተፈጥሮ ራሷ እንደምታጠፋው ይናገራል።

### 9. ጊዜን መለኪያና መቁጠሪያውን በትክክል ማወቅ

ለሰው ልጅ ጊዜ ራሱን የቻለ ታላቅ ስጦታ ነው።

- ነገርን ሁሉ በጊዜው ውብ አድርጎ ሰራው።
- ለሁሉም ጊዜ አለው።

- ጊዜ ወርቅ ነው ካለፈ አይመለስም
- በጊዜህ ወይም በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ።

እነዚህ ስለጊዜ ከተነገሩት መካከል ናቸው።

ከሰዓት መቁጠሪያ ጀምሮ እስከ ቀን ሳምንት ወርና ወቅት ዓመትም ሁሉ በሚገባ ትክክለኛውን ቆጠራ በማወቅ በዚያ መሰረት ስጋዊ፣ማንፈሳዊ ስራን መስራት ነው ክብረ በዓላትንም የምስጋና ቀናትንና ሰዓታትንም በሚገባ አውቆ በሰአቱ መጠቀም ነው።

### 10. የራስን መክሊት ፈልጎ ማግኘት

ሁሉም ሰው የየራሱ የሆነ መክሊትና ስጦታ አለው። አንድ መክሊት የተሰጠው አለ፣ሁለት መክሊትም የተሰጠውም አለ፣ አምስት መክሊትም የተሰጡት አሉ። ነገር ግን ሁሉም በተሰጠው ልክ ሁለት አራትና አስር ማትረፍ/የሰጠውን ፈጣሪውን በማገልገል እንጂ ቀብሮ ባለማስቀመጥ ሊኖር ይገባል።

መክሊት ሲባልም በስጋዊም፣በመንፈሳዊም ሊሆን ይችላል የራስን ስጦታ ማክበርና ያንንም ማስተማር/በዚያ ማገልገል የጎሊና እርካታ የስራ ስኬትና የተገልጋይንም ደስታ በሚገባ ያስታርቃል።

### 11. ለእውነተኛው አምላክ በእምነት ዘወትር ምስጋና ማቅረብ

ከእንቅልፍ ሰዓት ከነቃንበት ጀምሮ ዘወትር በኅሊናችንና በልባችን ቀናትን ቀድሶና ባርኮ ለሰጠን አምላክ ምስጋና ማቅረብ፡ ስራ ስንጀምርም ሆነ ስንጨርስ፣ ጉባዔ፣ስብሰባ፣ልማት፣እርሻ፣ትራንስፖርት በሁሉም መስክ ዘወትር በህሊናችን ምስጋናው ሊኖር ይገባል። በታወቁ ሰዓታትና ቀናት ደግሞ ህዝባዊ የምስጋናና መንፈሳዊ ዝግጅቶች ይኖራሉ ማለት ነው።

### 12. ፍቅር ለፈጣሪ ለሰው ልጅ ለእንስሳት እንዲሁም ለፍጥረታት በሙሉ

ተራራን ባፈልስ ባህርንም ብከፍል እምነት ኖሮኝ ብዙ ድንቅ ድንቅ ስራዎችን ብሰራ ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮህ ብረት ባዶ ነኝ እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ፣ ፍቅር የነገር ሁሉ ፍፃሚሜና መቋጫ ነው።

<<ኃያል ወልድን ፍቅር ከዙፋኑ ሳበው...................... እስከሞትም አደረሰው>>

የማስመሰል ሳይሆን ልባዊ የሆነ ፍቅር ለፈጣሪ፣ለወዳጆቹ ቅዱሳን፣ ለሰው ልጆች፣ለእንስሳትና ለፍጥረታት በሙሉ ያልተፃፈ የሕግ መደምደሚያዋ ይሆናል ማለት ነው የዚህች የብርሃን ሀገር።

## አንድ የብርሃን በርና አስራ ሁለት ድንቅ መስኮቶች ያሏት

<<በዋነኛው በር የሚመጣ እርሱ የበጎች ጠባቂ ነው በጎሮ በር የሚመጣ ግን እርሱ ነጣቂ ተኩላ ነው።>>

የዚህች ሀገር መግቢያዋ አንድ ነው ይህም የተመሰረተችበትን ዓላማ ሕግና ስርዓት አምኖ ተቀብሎ ማክበር ተገዢም መሆን። ይህን ለሚያደርግ ሁሉ ቤቱ ነው ለሚያምፅ ግን አይደለም።

አስራ ሁለቱ ድንቅ መስኮቶቿም በአስራ ሁለቱ ግድግዳዎች ያሉ ፍሬያቸውንና ስጦታዎችን መመልከቻና ማሳያ ናቸው።

## የተዋበና ያጌጠ ክዳኗ

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ቀደም ባለው ክፍል እንዳየነው ለክብር እንጂ ለውርደትና ለኃሳር ወይም ለመከራ አይደለም። ስለዚህ የዚህች ብርሃን ሀገር ክዳኗ ወይም አጨራረሷ የስጋ፣የመንፈስና የነፍስ በረከትን ማግኘት ፍሬን ማፍራት ነው።

## ማጠቃለያ

በእያንዳንዱ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በስፋትና በጥልቀት ብዙ ነገር ማለት መዳሰ  ይቻላል ነገር ግን የዚህ ፅሁፍ ዓላማ በአንድ ደካማ ሰው ብቻ ሙሉ የዚህችን ሀገር መመሪያና መተዳደሪያ ማውጣት ፖሊሲም ማዘጋጀት ሳይሆን እንደ አምላክ ፈቃድ የታየኝንና ዘወትር ጥያቄ የሆነብኝን የዓለም አኗኗር ወደ ጨለማ የሚሄደውን የዓለም ጉዞ ቀልብሶ ወደ ብርሃን መንገድ እንደሚመራ በማመን በሀገራችን በቀጣይ የምትመሰረተው ሀገርና መንግስት ምን መምሰል እንደሚገባትና በአሁኑ ሰዓት ትውልዱ በኢትዮጵያ አሳቢና መካሪ ጠባቂም አጥቶ በተስፋ መቁረጥ ውስጥ በመግባት ዘወትር ስንወጣና ስንገባ የምናየው የምንሰማው ነገር ሁሉ ለኅሊና የሚከብድ ነው። ይህ ሁሉ ደግሞ የተሰራው ኃጢያትችንና መተላለፋችን በከፈተው ክፍተት የጨለማው መንፈስ ባሮችና አምላኪዎች ተገዢዎች ገብተው በሴራ የተሰራ ስለሆነ አባታቸው የተባለ የሀሰት አባት እውነቱ ሲገለጥ ብርሃን ሲወጣ በጨለማ የሰራው ሁሉ ስለሚገለጥ ትቷቸው ራሱን ለማዳን ይፈረጥጣል ያኔ እነርሱም መግቢያ የላቸውም። ያኔ የብርሃን ልጆች ይገለጣሉ በእውነት የሚመላለሱ።

እስከዚያው እስከቀረችው ትንሽ ጊዜ ድረስ ግን ህዝብ በጋራ ይቁም ተስፋ ለቆረጡት ተስፋ ይስጥ፣የወደቀ ይርዳ፣ እግዚአብሔርን በመፍራት ሰብዓዊነትን በማስቀደም በጎ ይስራ የክፉ አጋንንትን ስራ ዝሙት፣ግብረ ሰዶም፣ ወዘተ ይቃወም። በፀሎት ይትጋ እንዲህ ሲሆን መከራው ያጥራል። ተስፋችንም ደግሞ ይፈጥነናል።

ምን አለፋን የብርሃን ሀገርን ስንኖርባት እንጂ በመስማት ስለማንረዳት አሁንም ደግሜ <<**ጽድቁንና መንግስቱን ፈልጉ ሌላው ይጨመርላችኋል።**>> በማለት ከኀጢያትና ከሀሰት ስራ በቀር ሁሉ ተፈቅዶልናል ካወቅንበት እላለሁ።

ምስጋና አነሳስቶ ላስጀመረኝና ላስፈፀመኝ ለልዑል እግዚአብሔር ይሁን።